# ደንብ

## የሞንትጎሞሪካውንቲፐብሊክስኩልስ

ተዛማጅ ሠነዶች፦ ACF, ACF-RA, ACH, ACH-RA, ACI, ACI-RA, BBB, BLB, COB-RA, ECC-RA, GCA-RA, GJC-RA, GKA-RA, JHC, JHC-RA

ኃላፊነት የሚመለከተው ዲቪዥን፦ Division of Human Resources and Talent Management

## የሰራተኛ ስነምግባር ጉድለት ተጠርጣሪነት ክስ ምርመራ

I. ዓላማ

A. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የውስጥ ምርመራ ዓላማና መጠነ ስፋት ለመመሥረት ሲሆን ይህም የሚሆነው፦

1. ቁልፍ የሆኑ እውነታዎችን የሚያረጋግጥ፣ በማስረጃ የተደገፉ ክፍተቶችን ለመፍታት መረጃ የሚሰበስብ እና ግድፈቶችን ወይም አለመግባባቶችን የሚፈታ ጥልቅ እና ተጨባጭ ምርመራ በማድረግ የጥፋተኝነት ክስን ለማረጋገጥ የሚያስችል በቂ ማስረጃ መኖር አለመኖሩን ለመወሰን፤

2. ለምርመራ ግኝቶቹ ተገቢ በሆነ መልኩ ሊሆኑ የሚችሉ የዲሲፕሊን እርምጃዎችን ለመወሰን ጥቅም ላይ የሚውሉ ግኝቶችን ለማመላከት ሲሆን፤ ሆኖም ግን መርማሪዎች የዲሲፕሊን እርምጃዎቹ ምን መሆን እንዳለባቸው አይወስኑም፤ እና

3. ከዚህ ደንብ ገደብ ውጭ የሆኑ በሌሎች MCPS ደንቦች ውስጥ ሙሉ በሙሉ የተካተቱ የማጣቀሻ ሪፖርት ማድረጊያ ሂደቶች

B. ከሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ (ቦርድ) ፖሊሲ GCB፣ *የሰራተኛ ጥሰት ክሶችን መመርመር ጋር* በሚስማማ መልኩ MCPS በሰራተኞች የተፈጸሙ የጥፋት ክሶችን ለመመርመር ኃላፊነቶችን እና ሂደቶችን ማቋቋም ነው።

II. ትርጉም

A. *የውጭ ኤጀንሲማለት*፦ በዚህ ደንብ ዓላማ የስቴት እና የካውንቲ የሕግ አስከባሪ ኤጀንሲዎችን ማለት ሲሆን የሞንትጎመሪ ካውንቲ ስቴት አቃቤ ህግ ቢሮ የልዩ ተጎጂዎች ምርመራ ክፍል (SVID) ጭምር፤ በተለምዶ የህጻናት ጥበቃ አገልግሎት (CPS) በመባል የሚታወቀው በሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ (MCDHHS) ውስጥ የሚገኝ የህፃናት ደህንነት አገልግሎት፤ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የፖሊስ መምሪያ (MCPD) እና ሌሎች የከተማ አስተዳደር የህግ አስከባሪ ኤጀንሲዎችን ያካትታል።

B. *የውስጥ ምርመራ ማለት*፦ በሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ወይም በትምህርት ቦርድ የውስጥ ኦዲት ክፍል (IAU) የሚካሄድ ምርመራ ማለት ነው። የውስጥ ምርመራ ሂደት በውጭ ኤጀንሲ በሚደረግ የምርመራ ሂደት ላይ ጣልቃ መግባት ወይም ማደናቀፍ አይችልም።

C. *የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ* (MCPS) *ደንቦችማለት*፦ በቦርድ ፖሊሲዎች እና በዋና ዋና

እሴቶች፣MCPS ደንቦች እና በሞንትጎሞሪ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ *የሰራተኞች የስነምግባር ህግ ላይ የተቀመጡ መስፈርቶች እና የስነምግባር ደረጃዎች ማለት ነው።*

D. *መጥፎ ምግባር ማለት፡-* የሰራተኛ MCPS ደንብ ጥሰት ማለት ነው።

III. የውጭ ኤጀንሲ ምርመራዎች

A. የመግባቢያ ስምምነት

1. MCPS የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞችን የሚመለከቱ የተወሰኑ የክስ ምርመራዎችን ለማድረግ የትኛው ኤጀንሲ ቅድሚያ እንደሚሰጠው የሚያረጋግጡ የውጭ የህግ አስከባሪ ኤጀንሲዎች ጋር የመግባቢያ ስምምነቶችን (MOU) በመመሥረት ተግባራዊ ያደርጋል።

2. በሜሪላንድ ሕግ መሠረት፣ የሕግ አስከባሪ ኤጀንሲዎች የወንጀል ድርጊትን ወይም በልጆች ወይም ተጋላጭ በሆኑ አዋቂዎች ላይ የተጠረጠረ በደል ወይም ቸልተኝነትን የሚያካትቱ ክሶችን ለመመርመር ኃላፊነት አለባቸው።

3. የሰው ሀብት እና የሙያ ችሎታ አስተዳደር ክፍል (DHRTM)፣ሥርዓት የማስከበር እና የምርመራ መምሪያ (DCI)፣ የውጭ ምርመራ በሚካሄድበት ጊዜ የተማሪዎችን ወይም የሰራተኞችን ደህንነት ለማረጋገጥ ወይም ማስረጃዎችን ለመጠበቅ የሚያስፈልጉ ጊዜያዊ እርምጃዎችን በተመለከተ መካሄድ ስላለበት የውጭ ምርመራ ከዋናው ኤጀንሲ ጋር መማከር አለበት።

4. MCPS ከውጭ ኤጀንሲው ጋር አስቀድሞ ስምምነት ሳይደረግ እና ማንኛውም ገደብ ሳይደረግ ምስክሮችን፣ተጎጂዎችን፣ ወይም በተጠርጣሪነት ተጠያቂዎችን የምርመራ ቃለ መጠይቅ ማድረግ አይችልም።

5. አንድ የውጭ ኤጀንሲ MOU ውል መሠረት በምርመራው ውስጥ እንደ መሪ ሆኖ ኃላፊነቱን ከተረከበ በኋላ፣ ኤጀንሲው ምርመራው እስኪጠናቀቅ ድረስ መሪ ሆኖ ይቆያል። MCPS የውስጥ ምርመራ መጀመር የሚችለው ዋናው የውጭ መርማሪ ኤጀንሲ DCI በጽሑፍ ሲያሳውቅ ብቻ ነው።

IV. MCPS የውስጥ ምርመራዎች

የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞችን የህግ ጥሰት በተመለከተ የቀረቡ ክሶችን ውስጣዊ ምርመራ በማካሄድ ወይም በማስተባበር ረገድ DCI በዋናነት ኃላፊነት አለበት።

A. ወደ MCPS የሚቀርብ የተጠናቀቀ የውጭ ምርመራ

1. MCPS ከውጭ ኤጀንሲዎች ጋር የሚኖረውን ውጤታማ ግንኙነት ለመደገፍ MOU ጋር ከሚሳተፉ የሕግ አስከባሪ ኤጀንሲዎች መደበኛ መግለጫዎች ላይ አብሮ መሳተፍ አለበት።

2. ሰክሽን IV.B እንደተመለከተው MCPS ሰራተኞችን የህግ ጥሰት የውጭ ኤጀንሲ የሚያከናውናቸው ምርመራዎች በሙሉ እንዴት እንደተፈቱ ይገመግማል፤ እንዲሁም ከዚህ በታች በተጠቀሱት MCPS የሥራ ክፍሎች ወይም DCI በኩል ተጨማሪ ምርመራ እንዲደረግ ያደርጋል።

B. ለሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የቀረቡ ወደ MCPS የሥራ ክፍሎች ሪፖርት የተደረጉ

የክስ መዝገቦች

1. የሚከተሉት የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንቦች የሰራተኞች የጥቅም ግጭት፣በስራ ቦታ የጉልበተኝነት ጥሰት እና ትንኮሳ እና ሌሎች ጉዳዮችን ጨምሮ ሪፖርት የማድረግ ሂደቶችን ያገልጻሉ።

   a) እነዚህ ደንቦች የተወሰኑ MCPS የሥራ ክፍሎችን ጥያቄዎችን፣ ስጋቶችን፣ ወይም የጥሰቶችን ሪፖርቶች የሚያቀርቡ ግለሰቦች በመጀመሪያ ማግኘት እንዳለባቸው ይመድባሉ፡-

      1) ደንብ ACA-RA፣ *ከኢደሎአዊነት የነፃ፣ ፍትኃዊነት እና የብቃት ባህል*

      2) ደንብ ACF-RA፣ *ታይትል* IX *የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ* (MCPS) *ተማሪዎች የጾታዊ ትንኮሳ ምርመራ*

      3) ደንብ ACH-RA፣ *በስራ ቦታ የጉልበተኝነት ጥሰት*

      4) ደንብ ACI-RA፣ MCPS *የሰራተኞች* Title IX *ወሲባዊ ጥቃት ወይም ትንኮሳ ምርመራ*

      5) ደንብ GCA-RA፣ *የሰራተኛ የጥቅም ግጭት*

      6) ደንብ JHC-RA፣ *ስለ ህፃናት ጥቃት እና ቸልተኝነት ሪፖርት ማድረግ እና ምርመራ*

      7) ደንብ JHF-RA፣ *የተማሪ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራራት*

      8) ደንብ JHG-RA፣ *ወንበዴዎች፣ የውንብድና ተግባር፣ ወይም ሌላ ተመሳሳይ ጥፋት ወይም ህገወጥ የቡድን ጥሰቶችን መከላከል*

   b) እነዚህን ደንቦች መጣስ ሪፖርት የተደረጉ የሰራተኞችን ጥፋት የሚመለከቱ ክሶችን ስለሚያካትቱ፣ ሪፖርቱ ተቀባዩ ተጨማሪ ምላሾችን ለመወሰን DCI ጋር መተባበር አለበት።

   c) የስነምግባር ጥፋተኝነት ክስ ሲቀርብ፣ MOU መሠረት ክሱ ወደ ሕግ አስከባሪ ኤጀንሲዎች መተላለፍ ወይም መመራት ያስፈልግ እንደሆነ DCI መወሰን ይኖርበታል።

2. ግለሰቦች የስነምግባር ጥሰቶችን ሪፖርት መድረስ ወዳለበት የውጭ ኤጀንሲዎች፣ ለምሳሌ፡- "Lighthouse Hotline, Safe Schools Maryland Hotline, and the Montgomery County Office of the Inspector General" ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ። DCI ከትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት፣ ከትምህርት ቦርድ ጽ/ቤት እና MCPS የደህንነት እና የአደጋ መከላከል አስተዳደር ክፍል ጋር በቅርበት በመተባበር ከውጭ የሪፖርት ምንጮች የሚደረገውን ግንኙነት ያመቻቻል።

3. የመርማሪ ምደባ

   a) DCI ዳይሬክተር ለዋና መርማሪነት የሚያስፈልገውን ባለሙያ የመምረጥ፣ የመወሰን እና የመመደብ ኃላፊነት አለበት።

b) በሚከተሉት ሁኔታዎች፣ ምርመራው ከ DCI ሰራተኛ ውጭ እንደሚከተለው ለሌላ መርማሪ ሊሰጥ ይችላል።

1) የትምህርት ቦርድ የውስጥ ኦዲቲንግ ክፍል (IAU) ክሶች ከገንዘብ ብልሹነት ጋር በተያያዙ ጊዜ ውስጣዊ ምርመራ ለማድረግ ኃላፊነቱን ይወስዳል። የ IAU ቁጥጥር የሚሰጠው በቦርዱ/ተወካይ ነው።

2) DCI ዳይሬክተር ጋር በመመካከር፣ የሰራተኛ ተቆጣጣሪ በዲሲአይ ዳይሬክተር ቁጥጥር ስር ሆኖ በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ምርመራ እንዲደረግ ኃላፊነት ሊመደብለት ይችላል።

a. የተጠረጠረው ባህሪ በኮንፈረንስ ማጠቃለያ፣ በሪከርድ ማስታወሻ፣ ወይም በወቀሳ ሊፈታ የሚችል ከሆነ DCI ዳይሬክተሩ ምርመራውን ለሠራተኛው ሱፐርቫይዘር ሊመድብ ይችላል።

b. ቀደም ሲል የተፈፀመ ሌላ የዲሲፕሊን ታሪክ ካለ፣ ማንኛውም ሊሆን የሚችል አደጋ ወይም እገዳን የሚያከትል፣ ከሥራ ዝቅ ማድረግን ወይም ከሥራ መባረርን ሊያስከትል የሚችል ሁኔታ ካለ፣ ምርመራውን DCI ሠራተኞች እንዲያጣሩት ይመደባል።

3) በማስረጃ መረጋገጥ ያለበት ክሱ ተጨማሪ የባለሙያ እውቀት የሚፈልግ ከሆነ፣DCI ዳይሬክተሩ የምርመራውን ሂደት የሚደግፍ ወይም የሚመራ ከ DCI ውጭ የሆነ ብቁ መርማሪ ሊጠይቅ ይችላል።

c) በምንም አይነት ሁኔታ ቢሆን የሰራተኛን የተጠርጣሪነት ክስ በተናጥል ለመመርመር፣ ለመደራደር፣ ወይም በሌላ መንገድ ለመፍታት የምርመራ ሂደትን ለመምራት ኃላፊነት ያልተሰጠው ማንኛውም MCPS ሰራተኛ በምንም አይነት ሁኔታ ሊሰራ ወይም ጣልቃ መግባት አይችልም።

4. የጥቅም ግጭት

a) መርማሪዎቹ ገለልተኛ፣ ምክንያታዊ እና አድሎአዊነት የሌላቸው መሆን አለባቸው፣ እንዲሁም የምርመራውን ውጤት በተመለከተ አስቀድሞ አሉታዊ ግምት ሊኖራቸው አይገባም።

b) አንድ መርማሪ በምርመራው መጀመሪያ ላይ ወይም በሂደት ላይ እያለ የሚነሳ ማንኛውንም የጥቅም ግጭት ካለ (እውነተኛ፣ ሊሆን የሚችል፣ ወይም ለማድረግ የታቀደ) ወዲያውኑ መግለጽ አለበት፣ ይህም ከተጠርጣሪ ጥፋተኛ፣ በተጎጂነት ተጠርጣሪ ከሆነ አካል፣ ወይም ምስክር ወይም፣ በጥፋተኝነት ተጠርጣሪ ጋር ባለው የእዝ ሰንሰለት ውስጥ፣ በተጎጂነት ተጠርጣሪ ሰው ወይም ምስክር ጋር ያለውን ግንኙነት ጨምሮ፣ በመርማሪው ገለልተኝነት ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ወይም ሌሎች የምርመራውን ተጨባጭነት እንዲጠራጠሩ ሊያደርግ ይችላል ተብሎ የሚታሰብ ከሆነ ወዲያውኑ የማሳወቅ ግዴታ አለበት።

c) የጥቅም ግጭት ከተፈጠረ DCI ዳይሬክተሩ ምርመራውን ለሌላ መርማሪ እንደገና ይመድባል።

C. የምርመራ ሒደት

1. ምስጢራዊነት

መርማሪዎች የምርመራዎቻቸውን ሚስጥራዊነት በጥብቅ መጠበቅ አለባቸው። በምርመራው የተገኙ እውነታዎችን ማጋራት የምርመራውን ትክክለኛነት የማዛባት አደጋ ላይ የሚጥል ሲሆን አላስፈላጊ አድልዎ እና ብዥታን ሊፈጥር ይችላል።

2. ይፋ የማድረግ ግንኙነት

a) MCPS ተማሪዎች፣ ሰራተኞች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ሌሎች የማህበረሰቡ አባላት ለግላዊ ሁኔታዎች ምስጢራዊነት መጠበቅ የሚሰጡትን ዋጋ ይገነዘባል፣ እንዲሁም በፌዴራል እና በስቴት ህጎች መሰረት የተማሪ እና የሰራተኛ መረጃን ጥበቃ እና ተገቢ ባልሆነ ሁኔታ ይፋ እንደማይደረግ ሁሉንም ህጋዊ ግዴታዎች ያከብራል።

b) ከሠራተኞች፣ ከተማሪዎች ወይም ከማህበረሰቡ ጋር ስለ ምርመራ ሂደት የሚደረግ ማንኛውም ግንኙነት ምን ያህል የማደናቀፍ አደጋ እንደሚያስከትል ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት –

1) በፌዴራል ወይም በስቴት ሕግ መሠረት የተከለከሉ ሪከርዶችን ወይም ሪፖርቶችን ያለፈቃድ ይፋ ማድረግ፣

2) ከሕግ አስከባሪ ኤጀንሲ ጋር የተደረገ የመግባቢያ ስምምነትን የሚጥስ መሆኑን፣

3) በቀጣዩ ምርመራ ላይ ጣልቃ መግባትን እንደሚያስከትል፣ ወይም

4) በተጎጂነት የሚጠረጠረውን ሰው ጥቅም የሚጻረር መሆኑ ታሳቢ መደረግ አለበት።

c) በመካሄድ ላይ ስላለ DCI ምርመራ ግንኙነት የማድረግ ኃላፊነት የሚወሰነው በሱፐርኢንቴንደንት/ተወካይ ነው።

3. በሰነድ መያዝ

የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ GCB፣ *የሰራተኞችን ጥሰት የሚመለከቱ ክሶችን መመርመር፣* DHRTM የሰራተኞችን ጥሰት የሚመለከቱ ክሶችን በሙሉ ለመቀበል፣ ለመከታተል፣ ለመለየት እና ለመገምገም እንዲሁም የውስጥ ምርመራን ውጤቶች በሙሉ ለመጠበቅ DCI ደህንነቱ የተጠበቀ የጉዳይ አስተዳደር ውሂብ የማዘጋጀት ኃላፊነት አለበት።

D. ማንነትን ይፋ ሳይደረግ በሚስጥር የሚቀርቡ ቅሬታዎች ምርመራ

1. ማንነታቸውን ሳያሳውቁ የሚቀርቡ ቅሬታዎች በተጠቆሙት ተዛማጅ መረጃዎች ላይ በመመስረት ልክ ማንነታቸውን በመግለፅ ቅሬታ እንደሚያቀርቡት አይነት ተመሳሳይ ሂደቶችን በመከተል እና ጥልቅ የምርመራ ሂደትን በመጠቀም ምርመራ ይደረጋል።

2. ማንነታቸውን ከማያሳውቁ ግለሰቦች የሚቀርቡ ቅሬታዎች/ክሶች እና ማስረጃዎች ለሚመለከተው ሠራተኛ ይቀርባል፣ እና ምላሽ የመስጠት እድል ይሰጣቸዋል።

3. ማንነት ሳይገለጽ የሚቀርቡ ሪፖርቶች፣የምርመራ ውጤቶችን ለሪፖርት አድራጊው(ዋ) ምላሽ የመስጠት እድልን ይገድባል።

E. እውነተኛና ትክክለኛ መረጃን ይፋ የማድረግ ኃላፊነት

MCPS ደንብ GCA-RA *የሰራተኛ የጥቅም ግጭት* ላይ እንደተቀመጠው፣ ማንኛውም የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኛ ማንኛውም ኦዲት፣ ጥናት፣ ወይም ምርመራ ጋር በተያያዘ የተሳሳተ ወይም አሳሳች መረጃ መስጠት የጥቅም ግጭት ይሆናል።

F. ብቀላ

የሜሪላንድ “የጥቆማ/የማጋለጥ” ሕግን ሙሉ በሙሉ በማክበር፣ ቦርዱ በቅን ልቦና የሰራተኞችን ጥሰት የሚመለከቱ ወይም መረጃ የሚያቀርቡ ወይም በምርመራ ላይ የሚሳተፉ ግለሰቦችን የቀል እርምጃ እንዳይፈፀምባቸው ይከለክላል። MCPS በምርመራ ላይ ለሚሳተፉ ወገኖች በሙሉ (ለምሳሌ፡- መልስ ሰጪው(ዋ)፣ አቤቱታ አቅራቢው(ዋ) እና ማናቸውም ምስክሮች) የበቀል እርምጃ፣ ብቀላ፣ ወይም የሐሰት ክስ የዲሲፐሊን እርምጃ ሊወሰድባቸው እንደሚችል ያሳውቃል።

G. የምርመራ መጠናቀቅ/መዘጋት

1. በምርመራ የተገኙ ውጤቶች ዓይነት

   a) ያልተረጋገጠ – የተጠረጠረው ጥሰት እንዳልተከሰተ ወይም የምርመራ ውጤቱን ለመደገፍ የሚያስችል በቂ ማስረጃ እንደሌለ የሚያሳይ ግኝት ነው።

   b) የተረጋገጠ - ተጠርጣሪው(ዋ) በፈጸመ(ች)ው ጥሰት ምክንያት የቀረበውን ክስ የሚያረጋግጡ በቂ ማስረጃዎች እንዳሉ የሚያሳይ ግኝት ነው።

2. የጊዜ ማእቀፍ

   a) ክሱ በተለይ ውስብስብ በመሆኑ ወይም ሌሎች ግልጽ ያልሆኑ ሁኔታዎች ስላሉ ተጨማሪ ምርመራ ለማድረግ ተጨማሪ ጊዜ የሚያስፈልገው ካልሆነ በስተቀር፣45 የሥራ ቀናት ውስጥ DCI የምርመራ ውጤት ላይ መድረስ አለበት።

   b) 45 የሥራ ቀናት በላይ ማራዘሚያ የሚያስፈልግ ከሆነ፣ DCI ክሱን ከተቀበለ በኋላ ባሉት 30 የሥራ ቀናት ውስጥ ለሠራተኞች የሙያ አስተዳደር ኃላፊ ያሳውቃል።

   c) የሠራተኞች ሙያ አስተዳደር ኃላፊ ከትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት/ተወካይ ወይም ከህግ አገልግሎት ክፍል ኃላፊ ጋር ስለ ጉዳዩ ውስብስብነት ወይም አወዛጋቢ ሁኔታዎች ከተመካከረ በኋላ ከምርመራ መረጃ ሰጪዎች ጋር ተጨማሪ ግንኙነት ለማድረግ መመሪያ መስጠት አለበት።

3. የምርመራ ሪፖርት መዝገብ እና የመዝገብ ተረካቢዎች

   a) DCI የምርመራ ሪፖርት እና ደጋፊ ሰነዶችን የያዘ የምርመራ ሪፖርት መዝገብ ያዘጋጃል፣ ይህም DHRTM የሠራተኞች ሙያ አስተዳደር ኦፊሰር እንዲገመገም ይቀርባል።

   b) IAD በቀጥታ ለቦርዱ/ለተወካዩ ሪፖርት ያደርጋል እና የምርመራ ግኝቶቹን ለዋናው የሠራተኞች ሙያ አስተዳደር ኦፊሰር/ተወካይ ያሳውቃል።

   c) ቀጣይ ግምገማ እና DHRTM እርምጃ በድርድር ስምምነቶች ውስጥ የተገለጹ ከሆነ ከአስፈፃሚ አመራር ጋር ተጨማሪ ምክክር ሊያስፈልግ ይችላል። የሠራተኞች ሙያ አስተዳደር ኃላፊ ከምርመራው ጋር በተያያዘ ከሠራተኛው ጋር ስለሚኖረው ቀጣይ

ግንኙነት ለ DCI መመሪያ ይሰጣል።

4. ከሠራተኞች ሙያ አስተዳደር ኃላፊ የሚሰጠውን መመሪያ ተከትሎ፣ DCI ለሠራተኛው ምርመራው መጠናቀቁን ያሳውቃል እና ለቀጣይ እርምጃዎች የጊዜ ሰሌዳ ያስቀምጣል። MCPS በሰራተኛ ላይ የሚደረግ ማንኛውም የዲሲፕሊን እርምጃ የሚወሰነው በትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንቴንደንት/ተወካይ ስለሆነ ዝርዝሩ በዚህ ደንብ ላይ አልተገለፀም።

5. ሁሉም የምርመራ ሰነዶች በ DCI ደህንነቱ በተጠበቀ እና ሚስጥራዊ በሆነ የጉዳይ ክትትል ስርዓት ይቀመጣሉ። የምርመራው የዲሲፕሊን ውጤቶች በሠራተኛው መዝገብ ውስጥ የሚመዘገቡት ክሱ የተረጋገጠ ሲሆን ብቻ ነው።

I. ክለሳ እና ሪፖርት

አጠቃላይ የምርመራ መረጃ ለክትትል ዓላማ በየጊዜው ለትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ሪፖርት ይደረጋል።

***ተዛማጅ ምንጮች፡-*** Annotated Code of Maryland, Family Law Article, §5-706; Education Article, §6-901-906, Public School Employee Whistleblower Protection; Code of Maryland Regulations 07.02.07.02-.04, 13A.12.05.02, and 13A.12.06.02; Montgomery County Public Schools Employee Code of Conduct

*ስለ ደንቡ ታሪክ፦* አዲስ ደንብ፣ ኦክቶበር 1986፤ ሜይ 4, 2006 ተሻሽሏል፤ ኦክቶበር 15, 2025 ተሻሽሏል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፣ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል" ። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

በሜሪላንድ ስቴት የሚገኙ የህዝብ ትምህርት ቤቶች እና የህዝብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ት/ቤቶች በሙሉ የሚከተሉትን ህጎች በማክበር እንዲሠሩ የስቴቱ ፖሊሲ/ድንጋጌ ነው፡-

(1)የፌደራል ታይትል VI የዜጎች መብቶች ደንብ 1964፣ እና

(2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኼውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-

- (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
- (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
- (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

የግንኙነት መርጃዎች እና የፌደራል፣ የስቴት፣ ወይ የአካባቢ መስፈርቶች በተለያዩ ሕትመቶች መካከል ልዩነት ሊኖራቸው ስለሚችል በዚህኛው ህትመት ላይ የተካተተው የሚፀና መሆኑን ልብ ይበሉ። ወቅታዊ መረጃዎችን ለማግኘት እባክዎን ይህን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination.

| MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*** | MCPS ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ *** |
|---|---|
| Director of Student Conduct and Appeals<br>Division of Equity and Organizational Development<br>850 Hungerford Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Division of Human Resources and Talent Management<br>Department of Compliance and Investigations<br>15 West Gude Drive, Suite B400, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| 1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ |
| Section 504 Coordinator ሰክሽን 504 አስተባባሪ<br>Division of Specialized Support Services, Department of School Counseling<br>850 Hungerford Drive, Room 170, Rockville, MD 20850<br>240-987-8031 \| 504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Division of Human Resources and Talent Management<br>Department of Compliance and Investigations<br>15 West Gude Drive, Suite B400, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*** | |
| Title IX Coordinator<br>Division of Equity and Organizational Development, Department of Student Conduct and Appeals<br>850 Hungerford Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| TitleIX@mcpsmd.org | |

*ይህ ማሳወቂያ የተሻሻለውን የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተሟለጠ ነው።

**ይህ ማሳወቂያ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር ይሟለጣል።

***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል። U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), 61 Forsyth St. S.W., Suite 19T10, Atlanta, GA 30303, 404-974-9406 and TDD: 800-877-8339, OCR.Atlanta@ed.gov, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ"Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ኦክቶበር 2025